ታህሣሥ 23 ቀን 2010 ዓ.ም.

# “ሁለቱ - 29ኞች” ! !

ከታጋይ ሓዱሽ ካሡ

ከተማዋ አለወትሮዋ ደምቃለች፡፡ የአየር ፀባዩም ከደጋ እና ወይናደጋ ለመጡት የከተማ ታዳሚዎች ብዙ አላስቸገረም፡፡ የሰው ልጅ መገኛ፣ የተለያዩ የቱሪስት መስህብ ባለቤቷ እና የአፋር ክልል ዋና ከተማ ሰመራ በህዳር ወር 2010 ዓ.ም፣ የክልሉን ህዝብ ተጠቃሚ ያደረጉ የተለያዩ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ተቋማትን ግንባታ ወደ ሥራ በማስገባት ውበቷ ጨምሯል፡፡

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት፣ የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት እንዲሁም የኢፌዴሪ የመንግሥት ኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ምስጋና ይግባቸው እና፣ **“በሕገ-መንግሥታችን የደመቀ ሕብረ-ብሄራዊነታችን ለህዳሴአችን”!!** በሚል መሪ ቃል ለ12ኛ ጊዜ በአፋር - ሰመራ ከተማ የተከበረው የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀንን ከታደሙት አንዱ ነበርኩኝ፡፡ ዋናው በዓል ህዳር 29 ከመከበሩ በፊት በነበሩት ቀናት የተለያዩ በርካታ ፍፃሜዎች/events/ ተከናውነዋል - በሰመራ፡፡ ከእነዚህ አንዱ ህዳር 28/2010 ዓ.ም. የተደረገው ሲምፖዚየም ተጠቃሽ ነው፡፡ የህዳር 29 ትሩፋት የሆነው እና ሰመራ ከተማን የዘመናዊ ታላቅ ህንፃ ባለቤት እንድትሆን ባደረገው በዚሁ አዲስ አዳራሽ በተካሄደው ሲምፖዚየም በሁለት ምሁራን ማለትም **አቶ ዓለማየሁ እርቅይሁን እንግዳ እና አቶ ጋሻው መሐመድ ሞትማ** ተዘጋጅቶ የተፃፈው **“ዋለልኝ መኮንን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ መሪ”** የሚል መጽሐፍ በ100 ብር ተሸጧል፡፡ እኔም መጽሐፉን ገዝተው ካነበቡት አንዱ ለመሆን በቅቻለሁኝ፡፡ በዚህ አጋጣሚ በአራቱም ማዕዘናት ያሉት የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ በዋነኛነት ወጣቱ መጽሐፉን ገዝቶ ቢያነበው በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንዲሁም የዴሞክራሲ ኃይሎች

የትግል ታሪክ በአግባቡ ሊረዳ ይችላል የሚል ሙሉ እምነት እንዳለኝ ስገልፅ ድፍረት አይሆንብኝም፡፡

ተጨባጭ ማስረጃዎችን አሰባስቦ በግልፅ የአማርኛ ቋንቋ የተቀነባበረው ይኸው **"ዋለልኝ መኮንን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ መሪ"** የሚለው መጽሐፍ፣ በርካታ ቁምነገሮች የዳሰሰ ቢሆንም የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ግን በአንድ ጉዳይ ላይ ብቻ ትኩረት አድርጓል፡፡ ይኸውም አሁን ላለችው ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መመሥረት አንኳር ጉዳይ በሆነው ማለትም፤ በአጠቃላይ በ1959 ዓ.ም. በተመሠረተው የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበር /National union of Ethiopian University students/ ውስጥ ስር-ነቀል /Radical/ ለውጥ ፈላጊና ተራማጅ አስተሳሰብ የነበራቸው እነ ዋለልኝ እና ጥላሁን ግዛው የወቅቱን የኢትዮጵያ መሠረታዊ ችግሮች ለመፍታት ያደረጉት ተጋድሎ፣ **/በነገራችን ላይ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበር ለዘብተኛ እንዲሁም ስር ነቀል ለውጥ ፈላጊው እና ተራማጅ የሚባሉ ተማሪዎች ያቀፈ እንደነበረ ልብ ይሏል/** በዋነኛነት ደግሞ ስር ነቀል ለውጥ ፈላጊው እና ተራማጁ ምሁሩ ታጋይ የህዝብ ልጅ ዋለልኝ መኮንን በኢትዮጵያ የብሄርና ብሄረሰቦች ጥያቄ የነበረው የማያወላዳ አቋም ምን ይመስል እንደነበረ በደምሳሳው ለማስታወስ እና አሁንስ ምን ይደረግ የሚል ነገር በአጭሩ ለመጠቆም ነው፣ የዚህ ጽሑፍ አጠቃላይ መነሻና መድረሻ፡፡

በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ስር ነቀል ለውጥ ፈላጊና ተራማጅ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች በወቅቱ በኢትዮጵያ የነበሩ ዘርፈ ብዙ መሠረታዊ ችግሮች ማለትም፣ ፊውዳላዊ ሥርዓቱና የመሳፍንት ገዥ መደብ በአርብቶ አደሮች እና በአርሶ አደሮች ሲያካሂድ የነበረው አስከፊ ጭቆና፣ የመሬት ላራሹ ጉዳይ፣ የትምህርት ሥርዓትና ኢ-ፍትሃዊ ተደራሽነት፣ የማህበረ-ኢኮኖሚ ችግሮች፣ የፖለቲካ ነፃነት ጉዳይ፣ የጾታ እኩልነት፣ የሴቶች ጭቆና እና በትግል ወቅት የሴቶች ተሳትፎ፣ የቋንቋና የባህል የበላይነትና የበታችነት ሁኔታ፣ በአጭሩ የብሄሮችና ብሄረሰቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ጉዳይ መሠረታዊ መፍትሄ የሚሹ መሆናቸውን በአግባቡ ተገንዝበው ይታገሉ ነበር፡፡

“ከስር-ነቀል ለውጥ ፈላጊና ተራማጅ ተማሪዎች መካከል በኢትዮጵያ የብሔር ጥያቄ ችግሮችንና ፖለቲካዊ መፍትሄዎችን በመያዝ በአደባባይ ደፍሮ ለውይይት የቀረበው ዋለልኝ መኮንን ነበር፡፡ በዚህ አቋሙ ሀገሪቱ ከተዘፈቀችባቸው ዘርፈ ብዙ ችግሮች ውስጥ የብሄር ጥያቄ አንዱ መሆኑን ስለተገነዘበ ጉዳዩን ከድብብቆሽ ወሬ በግልጽ ለውይይት ወደ አደባባይ አቅርቦታል፡፡”

ይኸውም **“የብሄር ጥያቄ በኢትዮጵያ”** “ON THE QUESTION OF NATIONALITIES IN ETHIOPIA” በሚል ርዕስ ዋለልኝ መኮንን ያቀረበው ጽሑፍ በብዙ ተማሪዎችና በሀገሪቱ ሕዝቦች ላይ አዲስ ስሜትን ፈጥሯል፡፡ በኅዳር ወር 1961 ዓ.ም. ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ አዲስ ተማሪዎችን ለመቀበል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በልደት አዳራሽ በተዘጋጀው የ“እንኳን ደህና መጣችሁ” ፕሮግራም ላይ ዘውዳዊው የንጉሠ ነገሥቱ ሥርዓት በብሄሮች የማንነት ጥያቄ ዙሪያ ያሳደረውን ተጽዕኖ፣ በብሔሮች ነባራዊ ሁኔታና ወደፊት ሊሆን በሚገባው ፖለቲካዊ መፍትሔ ላይ ያተኮረ ጽሑፍ ዋለልኝ መኮንን ለውይይት አቅርቧል፡፡

ሰፊ የሆነ ውይይትና ክርክር ከተካሄደ በኋላም ጽሑፉ **“ታገል”** (Struggle) ይባል የነበረው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መጽሔት ላይ ታትሞ ወጥቷል፡፡ በብዙዎች ዘንድ የተለያየ ስሜትን የፈጠረው ይኸው የዋለልኝ መኮንን ጽሑፍ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ማለትም /ዋለልኝ መኮንን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ መሪ ዓለማየሁ እርቅይሁን እንግዳ እና ጋሻው መሐመድ ሞትማ ከገፅ 254-ገፅ267/ ባሉት ገፆች ያሰፈሩት ዋለልኝ መኮንን ጉዳዩን አስመልክቶ በእግሊዝኛ ቋንቋ ያዘጋጀው ትንተና እንዳለ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

ON THE QUESTION OF NATIONALITIES IN ETHIOPIA

By Walleligne Mekonnen

Arts IV, HSIU

Nov.17, 1969

"The main purpose of this article is to provoke discussions on the "sacred", yet very important issue of this country-the Question o Nationalities. The article as it was prepared for a special occasion (where detailed analysis was due time and other inconveniences impossible) suffers from generalizations and inadequate analysis. But I still feel it is not mediocre for a beginning.

I expect my readers to avoid the temptation of snatching phrases out of their context and capitalizing on them. Instead every point raised here should be examined in the light of the whole analysis.

We have reached a new stage in the development of the student movement, a level where Socialism as a student ideology has been taken for granted, and reaction with all its window dressing is on the defensive. The contradictory forces are no more revolution versus reform, but correct scientific Socialism versus perversion and faddism.

The Socialist forces in the student movement till now have found it very risky and inconvenient to bring into the open certain fundamental questions because of their fear of being misunderstood. One of the delicate issues which has not yet been resolved up to now is the question of Nationalities-some people call it ridiculously tribalism-but I prefer to call it nationalism. Panel discussions, articles in STRUGGLE and occasional speakers, clandestine leaflets and even tete-a-tete groups have not really delved into it seriously. Of course there was indeed the fear that it may alienate certain segments of the student population and as well the fear that the government may take advantage of an honest discussion to discredit the revolutionary student movement.

Starting from last year, a small minority began to discuss this delicate issue for the most part in secluded places. Discussions, even private, leak out and because they were not brought into the open they normally led to backbiting, misunderstanding and grossly exaggerated rumours. I think students are mature enough to face reality even if they are very sensitive. And the only solution to this degeneration, as witnessed from some perverted leaflets running amock [amok] these two weeks, is open discussion.

What are the Ethiopian people composed of? I stress on the word peoples because sociologically speaking at this stage Ethiopia is not really one nation. It is made up of a dozen nationalities with their own languages, ways of dressing, history, social organization and territorial entity. And what else is a nation? It is not made of a people with a particular tongue, particular ways of dressing, particular history, particular social and economic organization? Then may I conclude that in Ethiopia there is the Oromo Nation, the Tigrai Nation, the Amhara Nation, the Gurage Nation, the Sidama Natioln, the Wellamo [Wolayta] Nation, the Adere [Harari] Nation, and however much you may not like it the Somali Nation.

This is the true picture of Ethiopia. There is of course the fake Ethiopian Nationalism advanced by the ruling class and unwillingly accepted and even propagated by innocent fellow travelers.

What is this fake Nationalism? Is it not simply Amhara and to a certain extent Amhara-Tigre supremacy? Ask anybody what Ethiopian culture is? Ask anybody what Ethiopian language is? Ask anybody what Ethiopian music is? Ask anybody what the "national dress" is? It is either Amhara or Amhara-Tigre!!

To be a "genuine Ethiopian" one has to speak Amharic, to listen to Amharic music, to accept the Amhara-Tigre religion, Orthodox Christianity and to wear the Amhara-Tigre Shamma in international conferences. In some cases to be an

"Ethiopian", you will even have to change your name. In short to be an Ethiopian, you will have to wear an Amhara mask (to use Fanon's expression). Start asserting your national identity and you are automatically a tribalist, that is if you are not blessed to be born an Amhara. According to the constitution you will need Amharic to go to school, to get a job, to read books (however few) and even to listen to the new on Radio "Ethiopia" unless you are a Somali or an Eritrean in Asmara for obvious reasons.

To anybody who has got a nodding acquaintance with Marxism, culture is nothing more than the super-structure of an economic basis, So, cultural domination always presupposes economic subjugation. A clear example of economic subjugation would be the Amhara and to a certain extent Tigrai Neftyegna system in the South and the Amhara-Tigre Coalition in the urban areas. The usual pseudo-refutation of this analysis is the reference to the large Amhara and Tigrai masses wallowing in poverty in the countryside. For that matter during the heydays of British imperialism a large mass of British workers had to live under inhuman conditions.

Another popular counter argument is that there are two or three ministers of non amhara-tigre Nationality in the Cabinet, one or two generals in the army, one or two governors and a dozen balabats in the countryside. But out and out imperialists like the British used to rule their colonies mainly by enlisting the support of tribal chiefs, who were much more richer than the average citizen of the British Metropolis. The fact that (Houphet) Boigne and Senghor were members of the French National Assembly and the fact that they were even ministers did not reduce an iota of Senegalese and Ivory Coast [Ivoirians] loss of political independence.

Of course the economic and cultural subjugation by the Amharas and their junior partners the Tires is a historical accident. Amharas are not dominant because of

inherent imperialist tendencies. The Oromos could have done it, the wellamos [Wolaytas] could have done it and history proves they tried to do so, But that is not an excuse for the perpetuation of this situation. The immediate question is we must declare a stop to it. And we must build a genuine national state.

And what is this genuine national-state? It is a state in which all nationalities participate equally in state affairs, it is a state where every nationality is given equal opportunity to preserve and develop its language, its music and its history, It is a state where Amharas, Tigres, Oromos, Aderes[Harari], Somalis, Wollamos[Wolaytas], Gurages, etc. are treated equally. It is a state where no nation dominates another nation be it economically or culturally.

And how do we achieve this genuine democratic and egalitarian state?

Can we do it through military? No!! A military coup is nothing more but a change of personalities. It may be a bit more liberal than the existing regime but it can never resolve the contradiction between either classes or nationalities. The Neway brothers and Tadesse Birus could not have done it. Talking about Mengistu and Tadesse, one cannot fail to remember the reaction that the Mengistus coup though a family one and at that by a sector of Shoa Amharas(with few exceptions, of course among the Workeneh) was very popular just because it was staged by "Ethiopians"-Amharas. With Tadese, it was automatically a tribalist uprising. Why? Tadesse an Oromo cannot stage a nationalist coup but Oromo Supremacist.

I am not equivocal in condemning coups, but the Tadesse coup had at least one significant quality and a very important one too. It gave our Oromo Brothers and Sisters self-respect. And self-respect is an important pre-requisite for any mass-based revolution. Even the so-called revolutionaries, who scoffed at the coup just like the mass of the student body, could not comprehend this quality. You can clearly see in this instance the power of the Amhara-Tigre supremacist

[supremacist] feelings. They clearly proved that they were nothing more than the products of government propaganda on this question.

Can the Eritrean Liberation Front and the Bale armed struggle achieve our goal? Not with their present aims and set-up.

Both these movements are exclusive in character, led by the local Bourgeoisie in the first instance and the local feudal lords in the second. They do not have international outlook, which is essential for our goal. They are perfectly right in declaring that there is national oppression. We do not quarrel with them on this score. But their intention is to stop there. They do not try to expand their struggles to the other nationalities. They do not attempt to make a broad-based assault on the foundations of the existing regime. They deliberately try to forget the connection of their local ruling classes with the national oppression. In short these movements are not led by peasants and workers. Therefore, they are not Socialists; it would only be a change of masters for the masses. But for the Socialists the welfare of the masses comes first.

The same can be said for the Gojjam uprising. But I would like to take this opportunity once again to show how much Amhara supremacism [supremacism] is taken for granted in this Campus.

To applaud the ELF is a sin. If anything favorable is written out, it is automatically refuted by both USUAA and NUEUS. But the Gojjam affair was different. Support for it was practically a show of identity to the so-called revolutionaries.

Mind you, I am just saying that these movements are not lasting solutions for our goal-the set-up of a genuine Nationalist Socialist State. I am all for them, the ELF, the Bale movements, the Gojjam uprising, to the extent that they have challenged

and weakened the existing regime, and have created areas of discontent to be harnessed later on by a genuine Socialist revolution.

One thing again is certain. I do not oppose these movements just because they are secessionists. There is nothing wrong with secessionism as such. For that matter secession is much better than nationally oppressive government. I quote Lenin, "…People resort to secession only when national antagonisms make joint life absolutely intolerable and hinder any and all economic intercourse. In that case the interests of the freedom of the class struggle will be best served by Secession. I would also like to quote the resolution on the question of nationalities from the London International Socialist Congress of 1896 attended, supported and adopted by the Bolsheviks who brought about the October revolution, "This Congress declares that it stands for the full right of all nations to self-determination and expresses its sympathy for the workers and peasants of every country now suffering under the yoke of military, national or other absolutism."

As long as secession is led by the peasants and workers and believes in its internationalist obligation, it is not only to be supported but also militarily assisted. It is pure backwardness and selfishness to ask a people to be partners in being exploited till you can catch up. We should never dwell on the subject of secession, but whether it is progressive or reactionary. A socialist Eritrea and Bale would give a great impetus to the revolution in the country and could form an egalitarian and democratic basis for re-unification.

To come back to our central question: How can we form a genuine egalitarian national-state? It is clear that we can achieve this goal only through violence, through revolutionary armed struggle. But we must always guard ourselves against the pseudo-nationalist propaganda of the regime. The revolution can start anywhere. It can even be secessionist to begin with, as long as led by the

progressive forces-the peasants and the worker, and has the final aim the liberation of the Ethiopian Mass with due consideration to the economic and cultural independence of all the nationalities. It is the duty of every revolutionary to question whether a movement is Socialist or reactionary not whether a movement is secessionist or not. In the long run Socialism is internationalism and a Socialist movement will never remain secessionist for good.

To quote Lenin again, "From their daily experience the masses know perfectly well the value of geographical and economic ties and the advantages of a big market and a big state. "From this point of view of the struggle as well, a regime like ours harassed from corners is bound to collapse in a relatively short period of time. But when the degree of consciousness of the various nationalities is at different levels, it is not only the right but the duty of the most conscious nationality to first liberate itself and then assist others in the struggle for total liberation. Is that not true of Korea? We do support this movement, don't we? Then, what is this talk of tribalism, secessionism, etc…?"

ዋለልኝ በዚህ ጽሑፉ ኅብረ ብሔራዊነትን በማንጸባረቅ ኢትዮጵያ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝብ ሀገር ብቻ ሳትሆን ከደርዘን በላይ የሆኑ ብሔሮች ማለትም ትግሬዎች፣ ኦሮሞዎች፣ አደሬዎች፣ ሶማሌዎች፣ ወላይታዎች፣ ጉራጌዎች፣ ወዘተ የሚኖሩባት፣ የየራሳቸውን ቋንቋ፣ እምነት፣ ባህል፣ የማኅበረሰብ ዕሴቶች በውስጧ አቅፋ የያዘች መሆኗን በግልጽ ወደ አደበባይ ለውይይት ያቀረበ በመሆኑ ሁሌም በታሪክ ተጠቃሽ ያደርገዋል፡፡

"መብታቸውን ለማስከበር ጥያቄ የሚያነሱ ብሔሮች 'ጎሰኛ' የሚል ቅጽል ስም ይሰጣቸዋል፡፡ እኔ ግን ብሔርተኛ ተብዬ መጠራትን እመርጣለሁ፡፡" በማለት የማንነት ጥያቄን ማንሳት የጠባብነትና የጎሰኛነት አስተሳሰብ አለመሆኑን አስገንዝቧል፡፡ ዋለልኝ

**ይህንን ጽሑፍ በአደባባይ ለክርክርና ለውይይት ከማቅረቡ በፊት ስለብሔር ጥያቄና ፖለቲካዊ መፍትሔ ደፍሮ በግልጽ ለውይይት ያቀረበ አካል አልነበረም፡፡**




**ከላይ ካለው የስር-ነቀል ለውጥ ፈላጊውና ተራማጅ ምሁሩ ዋለልኝ መኮንን ጽሑፍ ማለት የሚቻለው፣ ዋለልኝ መኮንን የነበረውን ወቅታዊ ሃገራዊ ሁኔታ ከዓለም አቀፍ ጉዳዮች ጋር አገናዝቦ የመተንተንና መሠረታዊ ችግሮች የማየትና መፍትሄ የማስቀመጥ የፖለቲካ ብቃት፣ ህዝባዊ ወገንተኝነት፣ የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ላዕላዊ የስልጣን ባለቤት መሆናቸው፣ በአጠቃላይ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ልትቀጥል ከሆነም ህብረ-ብሄራዊነት** (Nation-state) **በአግባቡ ሥራ ላይ መዋል እንዳለበት ዋለልኝ መኮንን እና የትግል አጋሮቹ የህይወት መስዋዕትነት የከፈሉለትን ዓላማ፣ ባለፉት** 27 **ዓመታት በሃገራችን ተግባራዊ ሆኖ፣ ተጨባጭ ፍሬ እያፈራ መሆኑ ሲታይ፤ ዋለልኝና ጓዶቹ በኢትዮጵየ ታሪክ ለዘለዓለሙ ህያው ሆነው እንደሚኖሩ በጉልህ የሚያሳይ ነው፡፡ እዚህ ላይ ሳይገለፅ የማይታለፍ ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም**

**የዋለልኝ መኮንን የፖለቲካ ብቃቱና ሰፊ የአተናተን አድማሱ ብቻ ሳይሆን ምን ያህል መጽሐፍ አንባቢ እንደነበረ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ አዋቂነቱ ምን ያህል ጥልቅ እንደነበር የሚያመለክት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡** ከዚህ ሁላችንም በተለይ ወጣቱ ትውልድ መጽሐፍ የማንበብ ባህል ማሳደግ ከእነ ዋለልኝ መኮንን ተሞክሮ ቢወስድ የአስተሳሰብ አድማሱን አስፍቶ ከስሜታዊነትና አጉል እልህ ተላቆ **ምክንያታዊ አስተሳሰብ** (Rational thinking) እንዲያዳብር እገዛ ያደርግታል ቢባል ሃቁን መናገር እንጂ ክፋት አይኖረውም፡፡

ስር-ነቀል ለውጥ ፈላጊውና ተራማጁ ዋለልኝ መኮንን ለውድ ህይወቱ ሳይሳሳ ብዕርና ወረቀት ብቻ ይዞ ጨቋኙን ፊውዳል የኃይለሥላሴ ሥርዓት ዕድሜ እንዲያጥር ታሪክ የማይረሳው ገድል ፈፅሞ ክቡር መስዋዕትነት ከፍሏል፡፡ ይኸውም ዋለልኝ መኮንን እየታሰረና እየተፈታ በሀገር ውስጥ ይካሄድ የነበረውን ትግል በቁርጠኝነት እየመራ ከቆየ በኋላ ትግሉን ለማስቀጠል የሚያስችለውን የትግል ስልት በመቀየስ እንዲሁም በብሄር ጥያቄ ላይ ተመሳሳይ አቋም ከነበረው እና <u>"የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ድርጅት"</u> የሚል የፖለቲካ ፓርቲ ለመመስረት ዝግጅት ላይ የነበረውን በአልጄሪያ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ቡድን፣ ያደረገለትን ግብዣ ተቀብሎ፣ ከሌሎች ስድስት/6/ የትግል አጋሮች ጋር በመሆን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ መስመር ቁጥር 720 ቦይንግ ጄት አውሮፕላን ዕለተ ዓርብ ህዳር 29/1965 ዓ.ም. ጠልፈው ለ15 ደቂቃ አየር ላይ ከተንዡ በኋላ፣ አብራቸው ከነበረች ታደለች ኪዳነ-ማርየም በስተቀር፣ ዋለልኝ መኮንንን ጨምሮ ስድስቱ በአውሮፕላኑ ውስጥ የነበሩት በአፄ ኃ/ሥላሴ መንግሥት የፀጥታ ኃይሎች በተኮሱባቸው ጥይት የህይወት መስዋእትነት ከፍለዋል፡፡ ህዳር 29/1965 ዓ.ም. ከዋለልኝ ጋር መስዋዕት የከፈሉት ቆራጥ ታጋይ የህዝብ ልጆች፤ **1.ማርታ መብራህቱ 2.በላይ ታደሰ/መሐመድ ዑስማን መሐመድ/ 3.ጌታቸው ሃብቴ 4.ተስፋዬ በርጋ 5.ዮሐንስ ፈቃዱ የተባሉ ናቸው፡፡**

ከእነ ዋለልኝ መኮንን ቀደም ባሉት ዓመታት ማለትም "የቀድሞ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ/የአሁኑ የአዲስ አበባ/ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበር ፕሬዚዳንት እና የስር ነቀል ለውጥ ደጋፊ የነበረው ተማሪ ጥላሁን ግዛውም ታህሣሥ 18 ቀን 1961 ዓ.ም. በአፋኙ የኃ/ሥላሴ ሥርዓት ወታደሮች በተተኮሰ ጥይት ለሀገሩና ህዝቡ ክቡር መስዋዕትነት ከፍሏል፡፡ የጥላሁን

ግዛው ደቀመዛሙርት የነበሩት እና የጥላሁን ግዛውን መገደል ተከትሎ በተቃውሞ ከተሳተፉት መካከል **አበበ በርሀ፣ ስብሃቱ ውብነህ፣ ጀማል ያሲን** የተባሉት አንጋፋ ታጋይ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በአፄ ኃ/ሥላሴ መንግሥት ክብር ዘበኛ በተባለው ጦር ጥይት በደረሰባቸው ጭፍጨፋ ታሪክ የማይረሳው መስዋዕትነት ከፍለዋል፡፡ ጥቂት የማይባሉት ተማሪዎች ደግሞ ቆስለዋል፡፡

ከእነ ዋለልኝ እና ጥላሁን በፊት በነበሩት ዓመታትም፣ የፊውዳላዊውን የአፄ ኃ/ሥላሴ ሥርዓት በመቃወም፣ የትግራይ/የወያኔ አመፅ/ እና የጎጃም አርሶ አደሮች ፀረ-ምዝበራ የተቃውሞ እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም የባሌ፣ የጌዴኦ ወዘተ ህዝቦች የፀረ-ብሄራዊ ጭቆና ትግሎች በተካሄዱባቸው ወቅቶች ከፍተኛ የህይወት መስዋዕትነት ተከፍለዋል፡፡

በአጭሩ በአራቱም የኢትዮጵያ መዓዘናት የማያቋርጥ ትግል ያካሄዱት እንዲሁም እነ ጥላሁን ግዛውና ዋለልኝ መኮንን የመሳሰሉት ምርጥ የኢትዮጵያ ታጋዮች የከፈሉት መስዋዕትነት ከንቱ አልቀረም፡፡ ፊላጭ ቆራጩ መስፍናዊ የኃ/ሥላሴ ሥርዓት በመላ የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መራራ ትግልና መስዋዕትነት መስከረም 2/1967 ዓ.ም ከሥልጣኑ ተገረሰሰ፡፡ ሆኖም ወታደራዊ ፋሽስት ደርግ የህዝቡን ድል በጠመንጃ ነጥቆ መንበረ ሥልጣን ላይ ተቆናጠጠ፡፡ ነገር ግን ወታደራዊ ጁንታው የወቅቱን ሦስት መሠረታዊ ጥያቄዎች ማለትም የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የመከበር፣ የብሄርና ብሄረሰቦች ጥያቄ ተገቢ ምላሽ የማግኘት እንዲሁም በአጠቃላይ የማህበረ-ኢኮኖሚ /በዋነኛነት መሬት የአርሶ አደሩ የማድረግ ጉዳይ/ በተፈጥሮው የሚመልስ አልነበረም፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች በኢህአዴግ ጥላ ስር ተሰባስበው እና የእነ ዋለልኝ መኮንን ዓርማ አንግበው፣ የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ከጎናቸው አሰልፈው ለ17 ዓመታት ባካሄዱት መራራ ትግል፤ የፋሽስታዊ ወታደራዊ የደርግ ሥርዓት እና አፋኝ መዋቅሩ ላይመለስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ግንቦት 20/1983 ዓ.ም. ሥርዓተ ቀብሩ ተፈፅሟል፡፡

የደርግ ሥርዓት ከተገረሰሰ ከአራት/4/ ዓመት በኋላ ማለትም እነ ዋለልኝ መኮንን የህይወት መስዋዕትነት የከፈሉለት ትግል፣ ትክክለኛ ምላሽ ያስገኘ 11 ዓበይት ምዕራፎች እና 106 አንቀፆች ያሉት የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት ህዳር 29/1987 ዓ.ም. ፀደቀ፡፡ የኢትዮጵያ

ብሄር፣ብሄረሰቦችና ህዝቦችም የረዥም ጊዜ ትግልና የመስዋዕትነት ውጤቶቻቸው በሆነው ሕገ-መንግሥታቸው ዙሪያ ተሰባስበውና እጅ ለእጅ ተያይዘው ፀረ-ድህነት እና ኋላቀርነት ትግላቸውን አጧጧፉት፡፡

**እዚህ ላይ ሕገ-መንግሥቱ የፀደቀው ህዳር 29/1987 ዓ.ም. ነው፡፡ ዋለልኝ መኮንን የተሰዋው ደግሞ ህዳር 29/1965 ዓ.ም. ነው፡፡** ስለዚህ **ሕገ-መንግሥቱ የፀደቀው በኢትዮጵያ የብሄር ጥያቄ መፍትሄ ማግኘት አለበት ብሎ ሽንጡን ገትሮ ለተዋደቀውና የህይወት መስዋዕትነት የከፈለውን ዋለልኝ መኮንን የተሰዋበት ቀን ታሳቢ ተደርጎ?!! ወይስ በአጋጣሚ?!! ይህንን ጥያቄ በተመለከተ አሁን በህይወት ያሉት የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት ሲፀድቅ የሕገ-መንግሥት ጉባዔው አባላት የነበሩት /የሕገ-መንግሥት አባቶች/** ምላሽ ቢሰጡበት፣ የተነሳው ጥያቄ ትክክለኛ ምላሽ ያገኛል ብቻ ሳይሆን ጉዳዩ በውል ታውቆ በታሪክም ለዘለዓለም እየተከበረ እንዲኖር ያደርጋል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት 27 ዓመታት በተለይም ባለፉት 15 ዓመታት፣ ኢትዮጵያ ባለ ሁለት አሃዝ ዕድገት በማስመዝገብ፣ አገራችን በ100 ዓመት ያላስመዘገበችውን ድል በጣት በሚቆጠሩ ዓመታት አስመዝግባለች፡፡ በዓለም ፈጣን ዕድገት በማስመዝገብ ካሉት 10 አገራት ተርታም ተሰልፋለች፡፡ በአሁኑ ወቅትም ሃገራችን ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ችግሮች ቢያጋጥማትም፣ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ዕድገቷ ወደፊት ከመገስገስ አልተገታም፡፡ ይልቁኑ አሁንም ቢሆን ዋነኛ የውጭ ኢንቨስትመንት መዳረሻ ሆናለች፡፡ ይኸውም ኢትዮጵያ በያዝነው 2010 በጀት ዓመት ብቻ ማለትም ባለፉት ሦስት ወራት ብቻ 4.7 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ኢንቨስትመንት መሳብ ችላለች፡፡ ከቻይና፣ ህንድና ኔዘርላንድ የመጡ ባለሃብቶችም ሥራ ጀምረዋል፡፡ በርካታ ወጣቶችም የሥራ ዕድል አግኝተዋል፡፡ ኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት ወራት ከፍተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት መሳብ ከቻሉ ጥቂት የዓለማችን ሃገራት መካከል አንዷ ነች" ሲልም https/www.Journalducameroun.com ዘግቧል፡፡

በዚህ አጋጣሚ አንድ ነገር ማውሳቱ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ እነ ዋለልኝ መኮንን የብሄር፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብት ይከበር ሲሉ እንዲሁም በኢህአዴግ መሪነት በ17 ዓመታቱ

ፀረ-ደርግ ትግል በ100 ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች በከተማ እና በገጠር ውድ ህይወታቸውን የከፈሉት እና አካል ጉዳተኛ የሆኑት በስመ ብሄር፣ **ዘረኝነት፣ ጠባብነት፣ ትምክህት፣ አክራሪነት** ወዘተ እንዲስፋፉ አልነበረም፡፡ ይልቁንም እነዚህ የኪራይ ሰብሳቢነት መገለጫ የሆኑና ለኢትዮጵያ ህዝቦች ነቀርሳ የሆኑ የተበላሸ አስተሳሰብ የወለዳቸው እኩይ ተግባራት ተወግደው፣ የኢትዮጵያ ብሄር፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች በአገራቸው ኢትዮጵያ በእኩልነት፣ በመፈቃቀድና በዴሞክራሲያዊ አንድነት ላይ የተመሠረተ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት እንጂ፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት በየክልሉ፣ እንዲሁም በየዩኒቨርሲቲዎች እና የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳዎች ሳይቀር እየታየ ያለው ዓላማ የለሽ ረብሻ እና የዘረኝነት ቅስቀሳ፣ በጊዜው ሃይ ካልተባለ መዘዙ ለሁሉም የከፋ ነው፡፡

በተለይ ወጣቱ ትውልድ የእነ ዋለልኝን የትግል ታሪክ በአግባቡ ሊገነዘብ ይገባል፡፡ ባለፉት 27 ዓመታት የተሟላ ሰላም ሰፍኖባት የነበረችው አገራችን - ኢትዮጵያ፣ አሁንም፣ ነገም፣ ከነገ ወዲያም ሰላምዋን የመጠበቅ ጉዳይ የሁሉም ኢትዮጵያዊ፣ በዋነኛነት ደግሞ የወጣቱ ቀዳሚ አጀንዳ ሊሆን ይገባል፡፡ ለምን ቢባል ሰላም ከሌለ ህይወት የለም፡፡ በአጠቃላይ በወጣቱም ሆነ በተማሪው የሚነሱ ጥያቄዎችም ምላሽ አያገኙም፡፡ እነ ዋለልኝ መኮንን የተሰዉት ሰላም ለማስፈን፣ መልካም አስተዳደር ለማንገስ፣ ዴሞክራሲ ስር እንዲሰድ እንዲሁም ማህበረ-አኮኖሚ ልማት በኢትዮጵያ እንዲረጋገጥ ነበር፡፡ ወጣቱ ትውልድም የአባቶቹንና የእናቶቹን፣ የወንድሞቹንና እህቶቹን አርአያነት ተከትሎ ድህነትን ማስወገድ ኃላፊነቱ በትከሻው እንደወደቀ አውቆ ቀበቶውን ጠበቅ አድርጎ የመታገል ጊዜው አሁን ነው፡፡ በእርግጥ ወጣቱ የተለያዩ ጥያቄዎች አሉት፡፡ ወደፊትም ይኖሩታል፡፡ መጠየቅም ሆነ መቃወም መብቱ ነው፡፡ ነገር ግን ወጣቱም ሆነ ተማሪው መብቱን የሚያስከብረው እና ለጥያቄዎቹ ምላሽ የሚያገኘው በከንቱ እርስ በርስ በመገዳደል፣ ምንም የማያውቁ አገር ሰላም ነው ብለው ኑሮን ለማሸነፍ ቀንና ሌሊት የሚተጉ የንፁሃን ዜጎችን ህይወት በማጥፋት፣ በቢሊዮኖች ብር የሚቆጠር የህዝብና የአገር ንብረትና ሀብት በእሳት በማጋየት ሊሆን አይገባም፡፡

ይህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ  የወጣቱን ትክክለኛ ጥያቄዎች ጠልፈው የራሳቸውን አጀንዳ የሚያራምዱ የጥፋት ኃይሎች መሣሪያ ከመሆን አይዘልም፡፡ በአጭሩ እዚህም እዛም እየተስተዋሉ ያሉ ህግና ሥርዓት ያልተከተሉና ለሥርዓተ አልበኝነት በር የሚከፍቱ ድርጊቶች የኢትዮጵያን የውጭና የውስጥ ጠላቶች ይጠቅሙ እንደሆነ እንጂ የወጣቱን ችግር በፍፁም አይፈቱም፡፡ ስለሆነም ያለፈው አልፏል፡፡ ወጣቱ በሰከነ አግባብ ትምህርቱን ሳያስተጓጉል መብቱን ሊያስከብር ይገባል፡፡ በዋነኛነት በህዝብ ተመርጦ አገሪቱን እያስተዳደረ ያለው የኢህአዴግ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሃገሪቱ የተከሰተው ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ከታህሣሥ 3/2000 ዓ.ም. ጀምሮ ለተከታታይ 17 ቀናት ያካሄደውን ጥልቅ ግምገማ፣ መነሻ አድርጐ ያሳለፋቸውን ስምንት/8/ ነጥቦችን በአንክሮ ተገንዝቦ ለተግባራዊነቱ ሊረባረብ ይገባል፡፡ ለምን ቢባል እነዋለልኝ መኮንን ክቡር መዋዕትነት የከፈሉት መሠረታዊ ችግሮች እንዲፈቱ ነው፡፡ እናም የችግሮች መፍቻ ቁልፎች ቀማሪ ነበሩ፡፡ ስለዚህ አሁን ያለው ወጣትም የችግር ብቻ ሳይሆን የመፍትሄ አካል የመሆን ግዴታ እንዳለበት ሊታመንበት ይገባል፡፡ በአጭሩ የአሁኑ ወጣት በተለይም በትምህርት ገበታ ላይ ያለው ተማሪ የእነ ዋለልኝ መኮንን አርአያ ተከትሎ ሃገሩን ከድህነት አላቆ አዲስ ታሪክ ሊሠራ ይገባል፡፡ በየደረጃው ያለው የመንግሥት አካልም ተገቢነት ያላቸውን የወጣቱና የተማሪው ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ለምን እነ ዋለልኝ መኮንን የተሰዉት ፍትህ እንዲኖር፣ ሰላም እንዲሰፍን፣ ድህነት ከእነ ሰንኮፉ እንዲቀበር ነውና፡፡

በመጨረሻም ዋለልኝ መኮንን የተሰዋበት ህዳር 29/1965 ዓ.ም. እንዲሁም የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት የፀደቀበት ህዳር 29/1987 ዓ.ም. በጋራ የሚከበሩበት ሁኔታ ቢመቻች ዘለዓለማዊ ታሪክ በደማቸው ፅፈው ያለፉትን እንደነ ዋለልኝ መኮንን የመሰሉትን ታጋዮች ማስታወስ፣ እውነተኛ የታጋዮች ታሪክ ለትውልዶች ለማስተላለፍ የሚረዳ እንጂ ጉዳት አይኖረውም፡፡ ከዚህ ሌላ ጥላሁን ግዛው እና የትግል አጋሮቹ የተሰዉበት ታህሣሥ ወርም እንደነ ዋለልኝ መኮንን የሚታወስበት ሁኔታ ቢፈጠር መልካም ነው፡፡

ስለሆነም የሚመለከተው አካል በተለይ የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት ጉዳዩን ቢያስብበት ሳይሻል አይቀርም፡፡ ለምን ቢባል ዋለልኝ መኮንን የተሰዋበት ቀን ህዳር 29፣ የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት የፀደቀበት ደግሞ በተመሳሳይ ህዳር 29 ነውና፡፡ ስለዚህም ሁለቱ - 29ኞች መነሻቸውና መድረሻቸው አንድ ነው ቢባል ብዙ ላያከራክር ይችላል፡፡ በአጭሩ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች፣ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በዋነኛነት ወጣቱ ትውልድ የአሁኑ ህልውናው መሠረት የሆኑት **ሁለት - 29ኞችን** እንደ ዓይኑ ብሌን ሊጠብቃቸው ይገባል፡፡ እንዴትና ለምን ቢባል?! በሁለት የተለያዩ የዘመን ክፋዮች የተፈፀሙት **ሁለቱ - 29ኞች**፣ ኢትዮጵያ እየገነባችው ያለውን በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመሠረት ድንጋይ ናቸው እና፡፡!!

**በሌላ ጽሐፍ እስከምንገናኝ ድረስ ቸር ይግጠመን!!**

**=======================================///=================**

**====================**